# ጥራቱ የተገለጸ ዘር (Quality Declared Seed) ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ

የመመሪያ ቁጥር 839 /2007

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ሦስት ዋና ዋና (መደበኛ፣ ተሸጋጋሪና ኢ.መደበኛ) የዘር ሥርዓቶች አሉ፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት በየዓመቱ በመደበኛ የዘር ሥርዓት በኩል የሚቀርበው የዘር መጠን ከ20 በመቶኛ አይበልጥም፡፡ ነገር ግን በፍጥነት እያደገ የመጣውን የአርሶ አደሩን የምርጥ ዘር ፍላጎት በመደበኛ ሥርዓት በሚቀርበው ዘር ብቻ ማሟላት ባለመቻሉ በኢ.መደበኛ ስርዓት ተመርቶ የሚቀርበው ዘር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህ ዘር ግን ጥራቱን ጠብቆ ለአርሶ አደሩ ባለመቅረቡ ሃገሪቱ በምትፈልገውና በምትጠብቀው መልኩ ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል አላስቻለም፡፡

ጥራት ያለው የዘር አቅርቦት ለምርትና ምርታማነት ማደግና ብሎም ለአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት አስፈላጊ በመሆኑና ይህ ደግሞ በአንድ ጊዜ ለሁሉም አርሶ አደር ማዳረስ ቀላል ባለመሆኑ አርሶ አደሮች እንደ አቅማቸው በተለያየ ደረጃ የሚገኝ የዘር ጥራት እየተጠቀሙ በሂደት ከፍተኛ ጥራት ያለውን ዘር መጠቀም ወደሚችሉበት ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል ሥርዓት መቀየስ በማስፈለጉ ምክንያት በዘር አዋጁ መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አውጭው ባለሥልጣን

የግብርና ሚ/ር ስለ ዕፅዋት ዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 782/2005 አንቀፅ 27/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በአዋጁ የተደነገጉትን ለማስፈፀም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ጥራቱ የተገለጸ ዘር (Quality Declared Seed) ሥርዓት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 839/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

በአዋጁ ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ወይም ሐረግ በድጋሜ ትርጉም መሥጠት ሳያስፈልግ በዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛል፡፡

፩/ “መደበኛ የዘር ሥርዓት” ማለት በሀገሪቷ በወጣው የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የተመዘገበ የተሻሻለ ዝርያ ዘር በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት ሙሉ በሙሉ ከዝርያ ማጎልበት እስከ ግብይት ድረስ ቁጥጥር የሚደረግበት የአሠራር ሂደት ነው፡፡

፪/ “የተሸጋጋሪ /Intermediate/ የዘር ሥርዓት” ማለት በመደበኛውና በኢ-መደበኛው የዘር ሥርዓት መካከል የሚገኝ ሥርዓት ነው፡፡

፫/ “ኢ-መደበኛ የዘር ሥርዓት” ማለት የተመዘገበ ወይም የአካባቢ ዝርያ /ነባር ዝርያ/ በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም በወጣው የዘር ደረጃ (መስፈርት) መሠረት ቁጥጥር ሳይደረግበት አርሶ አደሩ እርስ በርስ የሚያደርገው የዘር ልውውጥ ሥርዓት ነው፤

፬/ “የሚመረትበትና የሚሠራጭበት አካባቢ” ማለት በአንድ ክልል ውስጥ ጥራቱ የተገለጸ ዘር እንዲመረትና እንዲሠራጭ ክልሉ ፈቃድ የሰጣቸው ዞኖችና ወረዳዎችን ያመለክታል፤

፭/ “ዘር አምራች” ማለት ጥራቱ የተገለጸ ዘር የሚያመርቱ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው የተደራጁ እና የተመዘገቡ ወይም የተመዘገቡ አርሶ አደሮች ናቸው፤

፮/ “የአካባቢ ዝርያ” ማለት በአንድ በተወሰነ ሥነ-ምህዳር ለረጅም ዓመታት ሲመረት የቆየ ዝርያ ማለት ነው፤

፯/ “የዘር ሎት” ማለት ወጥነት ያለው በአካል ሊለይ የሚችልና መጠኑ የታወቀ ዘር ነው፤

፰/ “ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሠርትፊኬሽን” ማለት ተዘጋጅቶ ከቀረበው የተገለጸ ዘር አሥር መቶኛው ህጋዊ የዘር ጥራት ቁጥጥር የሚደረግበት የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ነው፤

፱/ “የውስጥ የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር” ማለት ዘር አምራቹ የራሱን ማሳና የላቦራቶሪ ፍተሻን በራሱ ባለሙያዎች አማካኝነት በዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

፲/ “የውጭ የዕፅዋት ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ” ማለት የተመዘገቡ ዘር የሚያመርቱ አምራቾች በወጣው የመስክና የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርት መሠረት ጠብቀው ማባዛታቸውን የሚቆጣጠርና ማረጋገጫ የሚሰጥ ህጋዊ አካል ነው፤

፲፩/ “ኩታ ገጠም” ማለት በአንድ አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች ስምምነት ፈጥረው ያላቸውን መሬት በአንድ ሰብል እንዲሸፈን በማድረግ ዘር የሚያመርቱበት ማሣ ማለት ነው፤

፲፪/ "መለያ ምልክት" ማለት ማናቸውም በዘር መያዣ ላይና ውስጥ የዘሩን ምንነት ለመለየት የተቀመጠ ወይም የተለጠፈ የጽሑፍ ወይም የሥዕል መግለጫ ነው፤

፲፫/ "አነስተኛ ይዞታ" ማለት የመሬት ይዞታው ከአሥር ሄ/ር ያልበለጠ ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው፡-

፩/ ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገቡና የዘር ጥራት ደረጃ የወጣላቸው ሰብሎችና ዝርያዎች ላይ፤

፪/ አነስተኛ ይዞታ ባላቸውና በተመዘገቡ ወይም በኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደራጁና በተመዘገቡ ዘር አባዥ አካላት የተመረተ ዘር ላይ ነው፤

፫/ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1-2) የተገለጸው ጠቅላላ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የማይሆንባቸው፡-

ሀ/ የድቃይ ሰብል ዘር፣

ለ/ በአርሶ አደሩ መካከል የሚደረግ የዘር ልውውጥ፣

ሐ/ የደን ዘር፣

መ/ ለምርምር ሥራ የሚውል ዘር፣

ሠ/ በመደበኛው ሥርዓት በመንግሥት ወይም በግል ዘር አምራችነት በተመዘገቡ የሚመረት ዘር ላይ ነው፡፡

## 5. የመመሪያው ዓላማ

### 5.1 አጠቃላይ ዓላማ

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሥርዓትን በዘር ሥርዓቱ ውስጥ በመተግበርና ያለውን የሰውና የቴክኒክ ሀብት በመጠቀም፣ በተደራጁ ዘር አምራች አካላት ዘንድ የሚባዛውን ዘር ጥራት በመጠበቅና ለልማት እንዲውል በማሠራጨት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤

### 5.2 ዝርዝር ዓላማዎች

ሀ/ ጥራቱ የተገለጸ የዘር ሥርዓት ከመደበኛ ዘር ሥርዓቱ ጋር በተደጋጋፊ መልኩ ማስኬድ፣

ለ/ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችና የተደራጁ ዘር አምራች አካላትን በማሳተፍ ጥራቱን የጠበቀ ዘር በበቂ ዓይነት፣ መጠንና ወቅት እንዲቀርብ ለማድረግ፣

ሐ/ በመደበኛው የዘር ሥርዓት ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎች ጥራት ያለው ዘር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣

መ/ በኅብረተሰቡ በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊነት ያላቸውና የተሻለ ምርት መስጠት የሚችሉ በመደበኛው የዘር ሥርዓት ተደራሽ ያልሆኑ የአካባቢ ዝርያዎች ጥራት ያለው ዘር በማቅረብ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ፣

ሠ/ ህገ-ወጥ የዘር አቅርቦትና ሥርጭትን ለመቆጣጠር፡፡

## ክፍል ሁለት

## መርህ፣ ማዘጋጀት እና ጥራት ቁጥጥር

### 6. ጥራቱ የተገለጸ ዘር መርሆዎች/መግለጫዎች፣

፩/ አማራጭ የዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት የማመቻቸት፣

፪/ ከመደበኛው የዘር ሥርዓት ጎን ለጎን የሚሄድና መደበኛውን የዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥርዓትን አለመተካት፣

፫/ ከመደበኛው ሥርዓት በስፋት ያልተዳሰሱ የተለያዩ ሰብሎችን የማካተት፣

፬/ አዋጭ በሆነ መልኩ የዘር ጥራትን የማረጋገጥ፣

፭/ አብላጫውን የዘር ጥራት የማረጋገጥ ኃላፊነት ለአምራቹ የመስጠት፣

## 7. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ስለማዘጋጀት፣

ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማዘጋጀት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፡-

፩/ የዘር ማከማቻ መጋዘኑ ማሟላት ያለበትን መስፈርት በዕዝል 1 የተመለከተው ይሆናል፤

፪/ የዘር ማበጠሪያ ቢያንስ አነስተኛ የዘር ማበጠሪያ መሣሪያ ያለው ወይም በቂ የሰው ኃይል አሰማርቶ ማስበጠር የሚችል፣

፫/ አነስተኛ የማሸጊያ ማሽን ያለው ወይም ከሌላ አካል በኪራይ ወይም በትውስት ስለማግኘቱ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

፬/ በዘር ዝግጅት ቢያንስ የአንድ ሣምንት ሥልጠና ያገኘ ወይም በቂ ልምድ ያለው ከሆነ፡፡

## 8. ጥራት ስለመቆጣጠርና ማረጋገጥ፣

ጥራቱ የተገለጸ ዘርን ጥራት የማረጋገጥ ሥራ በአምራቹና ጥራትን ማረጋገጥ ኃላፊነት በተሰጠው የክልል ባለሥልጣን ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ አፈጻጸሙም የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ጥራቱ ለተገለጸ ዘር ሥርዓት ባወጣው ደረጃ መሠረት ይከናወናል፡፡

### 8.1 የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት

ማንኛውም ጥራቱ የተገለጸ ዘር አምራች የውስጥ የመስክና የላቦራቶሪ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

#### 8.1.1 የመስክ ጥራት ቁጥጥር

የመስክ ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ያለው ወይም በትውስት ማግኘት የሚችል ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) የሰብል ዘር ወለድ በሽታና አረምን ለመለየት የሚያስችል በሥዕል የተደገፈ ማኑዋል/ኮምፓንዲኒየም፣

ለ) አንድ ካሬ ሜትር ከእንጨት ወይም ከብረት የተሠራ ኳድራንት፣

ሐ) መቁጠሪያ (ካውንተር)፣

መ) ጂ.ፒ.ኤስ፣

ሠ) የዘር እርጥበት መለኪያ፣

ረ) አነስተኛ የማጉያ መነጽር፣

ሰ) በበሽታ የተጠቃ የተክል አካል ናሙና መያዣ ከረጢት /የወረቀት፣ ፕላስቲክ/፣

ሸ) አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ቁሳቁሶች፣

ቀ) የምድር ሚዛን (weighing balance)፡፡

8.1.2 በላቦራቶሪ የውስጥ ጥራት ቁጥጥር

በአምራቹ አቅም ሥራው የሚከናወን ከሆነ ቢያንስ የሚከተሉትን ማሟላት መቻል አለበት፣

ሀ) ራሱን የቻለና 9 ካሬ ሜትር ያለው ክፍል፣

ለ) የናሙና መውሰጃ መዋጥ (ትራየር)፣

ሐ) የዘር ንጽህና መሣሪያ ቁሳቁሶች እንደ አናሌቲካል ሚዛን፣ ጠረጴዛ፣ አጉሊ መነጽር፣ ፎርሴፕስ፣ ስፓቹላ፣

መ) የዘር ብቅለት መፈተሻ ቢያንስ አነስተኛ የዘር ማብቀያ ፕላስቲክ ሣህኖች /ቦውል/ ማሟላት የሚችል በራሱ አቅም ማሟላት የማይችል ከሆነ ግን የዘር ፍተሻ ላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጡ ከሚችሉ ተቋማት አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚቻል የሚያረጋግጥ ማስረጃ አግባብነት ካለው መ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8.2 የውጭ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት

8.2.1 የውጭ የመስክ የዘር ጥራት ቁጥጥር

ሀ) ጥራቱ የተገለጸን ዘር ጥራት ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ባወጣው መስፈርት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፣

ለ) በውጭ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም የሚካሄድ የማሣ ጥራት ቁጥጥር ሥራ ተፈጻሚ የሚሆነው አምራቹ ዘሩን ያመረተበት ጠቅላላ ማሣ ወጥ የሆነ አያያዝና እንክብካቤ እንዲሁም የውስጥ ጥራት ቁጥጥር እንደተደረገበት ታሳቢ በማድረግ ነው፣

ሐ) የውጭ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም በጥራቱ የተገለጸ ዘር ከተሸፈነው ማሣ ውስጥ 10 በመቶኛ በሚሆነው ማሣ ላይ ጥራት ቁጥጥር ይካሄዳል፣

መ) በአሥር መቶኛው የሚገኘው ውጤት /ማለፍም ሆነ መውደቅ/ በቀሪው ማሣ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ሠ/ የአስር በመቶኛው የጥራት ቁጥጥር ሂደት በመደበኛው የማሣ ጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጥ ሥርዓት መሠረት ይከናወናል፡፡

8.2.2 የውጭ የላቦራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ

ሀ) የዘር ናሙና የሚወሰደው የመስክ ጥራት አሟልቶ ካለፈ ማሣ የተመረተ ዘር ላይ ይሆናል፣

ለ) የዘር አከመቻቸት /ሎቲንግ/ እና ናሙና አወሳሰድ በዓለም አቀፉ የዘር ጥራት ፍተሻ ማኅበር /ISTA/ ደረጃዎች መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፣

ሐ) የውጭ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም ጥራቱ በተገለጸ ዘር ተዘጋጅቶ በሎት ከተደረደረው ውስጥ ከጠቅላላው ሎት 10 በመቶኛ ከሚሆነው ናሙና ይወስዳል፣

መ) የናሙና አወሳሰድና የላቦራቶሪ ፍተሻ ሂደቱ ከመደበኛው የሠርትፊኬሽን ሥርዓት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ሠ) በአሥር መቶኛው የሚገኘው ውጤት /ማለፍም ሆነ መውደቅ/ በቀሪው 90 በመቶኛው ሎት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣

ረ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ጥቅም ላይ ሳይውል ካደረ ናሙና የሚወሰደው ከሁሉም ሎቶች ይሆንና ውሳኔ የሚሰጠው ግን ጥራቱ በተገለጸ ዘር የጥራት ደረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ

### 9. ዝርያን ስለማስመዝገብ፣

፩/ በመደበኛው የዝርያ ለቀቃና ምዝገባ የሚለቀቁና የሚመዘገቡ ዝርያዎች አሠራር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረት የተፈቀደለት ዘር አባዥ አካል የአካባቢ ዝርያን ለማስመዝገብ የሚከተሉትን ሂደቶች ማለፍ ይጠበቅበታል፣

ሀ/ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ በአቅራቢያ ለሚገኝ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ማቅረብ፣

ለ/ አመልካቹ ዝርያን ለማስመዝገብ ማመልከቻውን ሞልቶ ለግብርና ሚኒስቴር በክልሉ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም አማካኝነት መላክ፣

ሐ/ ግብርና ሚ/ር የቀረበለትን ጥያቄ በመመዝገብ ለጠያቂው ወደሚቀርብ ምርምር ማዕከል የባህርይ መገለጫ ፍተሻ እንዲካሄድ ይልካል፣

መ/ የምርምር ማዕከሉ በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ለአካባቢው ዝርያው ለአንድ የሰብል ወቅት የባህርይ መገለጫ ፍተሻ በድግግሞሽ በአንድ ቦታ ላይ ያካሄዳል፣ አግባብነት ያለው የግብርና ምርምር ማዕከል የባህሪ መገለጫ ፍተሻ ሙከራ ያካሄዳል፣ ውጤቱንም ለዕፅዋት ዝርያ ለቀቃ ጥበቃ እና የዘር ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት ያቀርባል፣

ሠ/ በቀረበው ሪፖርት ላይ የብሔራዊ ዝርያ ለቀቃ ኮሚቴ ውሳኔ ይሰጥበታል፣

ረ/ በውሳኔው መሠረት የጸደቀው ዝርያ በዝርያ መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል፡፡

### 10. ስለብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ፣

የተገለጸ ዘር ለማምረት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ያስፈልጋል፡፡

፩/ በቡድን ወይም በማኅበር የተደራጁ አርሶ አደሮች መሆን አለባቸው፣

፪/ ህጋዊ ዘር አባዥ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ባላቸው አባላት የተደራጀ ወይም መሬት በኪራይ ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ የውል ሠነድ ማቅረብ የሚችል፣

፫/ የዘር ማሣው /የመሬቱ/ ተዳፋትነት ለዘር ማምረት አመቺ መሆኑ በባለሙያ የተረጋገጠ፣

፬/ አነስተኛ ኩታገጠም የማሣ ስፋትን በተመለከተ፡-

ሀ/ ለብርዕ ሰብሎች ቢያንስ 5 ሄክታር፣

ለ/ ለጥራጥሬና ለቅባት ሰብሎች ቢያንስ 3 ሄ/ር

ሐ/ ለአትክልት ዘር ኩታገጠም የሆነ ማሣ በአንድ አካባቢ ቢያንስ 1 ሄ/ር

መ/ ለኮረት (Bulb Tuber) ለቁርጥራጭ (ስኳር ድንች) ኩታ-ገጠም የሆነ ማሣ በአንድ አካባቢ ቢያንስ 2 ሄ/ር፣

ሠ/ ለፍራፍሬ እና ለአነቃቂ (ቡናና ሻይ) ሰብሎች መሠረተ-ግንድ (root stock) ቢያንስ 0.5 ሄ/ር፣

ረ/ ለመክተብ (እንቡጥ ወይም ሳዮን ለአፐል፣ ለማንጎ) ቢያንስ 5 እናት ተክል፣

ሰ/ ለኮርም (ለእንሰትና ለሙዝ) ቢያንስ 100 ተክል፣

ሸ/ ለቡና ዘር አቅራቢነት ከሆነ ቢያንስ 750 ተክል በቡድን፣

፭/ የዘር ማባዣ ማሣ ሊያሠራው የሚያስችል በቂ የእርሻ መሣሪያዎች ያለው፣

፮/ መስፈርቱን ያሟላ የዘር ማከማቻ መጋዘን ያለው ወይም በኪራይ ስለማግኘቱ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

፯/ የተደራጁት ዘር አምራች አርሶ አደሮች በዘር አመራረት የሠለጠነ የግብርና ባለሙያ የቀጠሩ ወይም ከአካባቢው ግብርና ጽ/ቤት ቀጣይ ድጋፍ እንደሚያገኙ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ፣

፰/ የውስጥ የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ያለው ወይም አገልግሎቱን ከሌላ አካል ስለማግኘቱ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡

## 11. ስለማሸግ፣ መለያ ምልክት ስለማድረግ፣ ስለመደርደርና ውጤት ስለማሳወቅ፣

11.1 ማሸግ

ሀ) ዘሩ ከተበጠረ በኋላ የአምራቹና የውጭ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ ተቋም መለያ ምልክቶችን ከውስጥና ከውጭ በማድረግ ይታሸጋል፣

ለ) ዘሩ ሲታሸግ መለያ ታጉን ለመቀየር የሚደረግ ማንኛውንም ዓይነት ተግባር በግልጽ የሚያሳውቅ መሆን አለበት፣

ሐ) ከረጢቱ የጥራት ደረጃውን የጠበቀና የድርጅቱን መለያ ዓርማ ያካተተ መሆን አለበት፡፡

11.2 መለያ ምልክት

11.2.1 መለያው የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) የአምራቹ ሥምና አድራሻ፣

ለ) የሰብል ዓይነትና ዝርያ፣

ሐ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር የሚል ጽሁፍ፣

መ) የብቃት ማረጋገጫ ሠርትፊኬት ቁጥር፣

ሠ) የዘር ደረጃ፣

ረ) የብቅለት መጠን በመቶኛ፣

ሰ) የዘር ንጽህና በመቶኛ፣

ሸ) የዘር እርጥበት መጠን በመቶኛ፣

ቀ) የተጣራ የዘር ክብደት፣

በ) የተመረተበት ዓመት፣

ተ) የታሸገበት ቀን፣

ቸ) የቆይታው ጊዜ፣

ነ) የሎት መለያ ቁጥር፣

ኘ) በኬሚካል የታሸ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ፣

11.2.2 የመለያ ምልክቶች አንዴ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ እንደገና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ሆነው መዘጋጀት አለባቸው፣

11.2.3 መለያዎች ሲዘጋጁ በቅርጽ ሬክታንግል ሆነው የሚከተሉትን የቀለም ቅንብር ሊይዙ ይገባል፡

ሀ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር አንደኛ ትውልድ መደቡ አረንጓዴ ቀለም፣

ለ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር ሁለተኛ ትውልድና ከዚያ በላይ መደቡ ሙሉ ለሙሉ ቢጫ ይሆናል፣

ሐ) ለሁሉም የዘር ደረጃ የመለያው አንዱ ጫፍ ከሌላው የሚለይ ቀለም ዝቅተኛው ርቀት 3 ሴ.ሜ በመጠበቅ በጥቁር ቀለም ይቀለማል፡፡

11.2.4 የሎት መለያ ቁጥር አጻጻፍ

ሀ) የተመረመረበት ዓመት፣

ለ) የድርጅቱ የምዝገባ ቁጥር፣

ሐ) የሰብል ዓይነት፣

መ) የማሣ ቁጥር፣

ሠ) የዘር ደረጃ፣

ረ) ተበጥሮ የተዘጋጀበት ቦታ፣

ሰ) የሎት ቁጥር ማካተት አለበት፡፡

11.2.5 የዘር ክምችት አደራደር /ሎቲንግ/

ሀ) የአንድ ሎት መጠን ዓለም አቀፉ የዘር ምርመራ ማኅበር /ISTA/ በተቀመጠው መስፈርት /standard/ በላይ መብለጥ የለበትም፣

ለ) ከወለሉ በላይ መደርደሪያ ወይም ርብራብ /Pallet/ መኖር አለበት፣

ሐ) የዘር አደራደሩ ለናሙና አወሳሰድ አመቺ መሆን አለበት፣ ይኸውም በግድግዳና በሎት መካከል፣ በየሎቱ መካከልም ያለው ርቀት ናሙና ለሚወስደው ሰው በቂ መዘዋወሪያ እንዲያገኝ የሚያስችል መሆን አለበት፣

መ) የአየር ዝውውር በመጋዘን ውስጥ እንዲኖር፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካል ለማጠንና ናሙና አወሳሰድን ቀለል ለማድረግ፡-

1. ከግድግዳ እስከ ድርድር 1 ሜ. እና በየድርድሮች መካከል 1 ሜ. መተላለፊያ መንገድ መኖር አለበት፣
2. በጣሪያውና በድርድሩ መካከል ሁልጊዜም የ1.5 ሜትር ክፍተት ሊኖር ይገባል፣
3. በሁሉም የመጋዘኑ ማዕዘን ብርሃንና አየር በቀላሉ የሚያስገባ መሆን አለበት፣
4. ለአየር ማስገቢያ እንዲሆኑ የተሠሩ መስኮቶች የብረት ወንፊት የተገጠመለት መሆን አለበት፡፡

11.2.6 ውጤት ስለማሳወቅ

ሀ) ከተዘጋጀው የዘር ሎት በኢንስፔክተሩ ናሙና ከተወሰደ በኋላ የላቦራቶሪ ፍተሻ ተደርጎ ውጤቱ ለዘር አምራቹ በደብዳቤ ይገለጻል፣

ለ) ውጤቱ ከመገለጹ በፊት ዘሩን ለተጠቃሚ መሸጥ /መሠራጨት/ የለበትም፣

ሐ) ከመስፈርቱ በታች የሆነ የዘር ሎት በውጤቱ ላይ ለዘርነት እንዳይውል ይገለጻል፣ ለተጠቃሚም መሠራጨት የለበትም፡፡

## 12. ጥራቱ የተገለጸ ዘር ስለማሠራጨት

፩/ አምራቹ የግል አርሶአደር ከሆነ ያመረተውን ዘር፡-

ሀ) በቀጥታ ለሌሎች አርሶ አደሮች የመሸጥ፣ ወይም

ለ) በአካባቢው ለሚኙና በህጋዊ ሁኔታ ለተደራጁ የገበሬዎች ኀብረት ሥራ ማኀበራት ማቅረብ ይችላል፣

፪/ በኅብረት ሥራ ማኅበር የሚመረት ዘር ከሆነ በቀጥታ ለአካባቢ አርሶ አደሮች ያሠራጫሉ፣

፫/ የሥርጭት መረጃ በተገቢው ሁኔታ መዝግቦ አግባብነት ላለው አካል በየወቅቱ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 13. የባለድርሻ አካላት ኃላፊነትና ተግባር

ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሲሰሩ ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ የእያንዳንዱ ኃላፊነትና ተግባር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

፩/ የፌዴራል ግ/ሚ/ር ዝርያ ለቀቃ፣ ጥበቃና የዘር ጥራት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት፣

ሀ) ጥራቱ በተገለጸ ዘር ሥርዓት ዘር ለማምረት የሚፈለጉ የአካባቢ ሰብል ዝርያዎች አመዘጋገብን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣

ለ) ጥራቱ በተገለጸ ዘር ሥርዓት እንዲመረቱ ውሳኔ ያገኙ የአካባቢ ሰብል ዝርያዎች የሚመዘገቡበትን የመረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣

ሐ) አንድ ዝርያ ጥራቱ በተገለጸ ዘር ሥርዓት እንዲመዘገብ የሚፈልጉ አካላትን ጥያቄ በተዘጋጀው ፎርም መሠረት መሞላቱን አረጋግጦ ይቀበላል፣

መ) እንዲመዘገብ የቀረበውን የአካባቢ ዝርያ ናሙና ዘር ተቀብሎና ተገቢውን ክፍያ አስከፍሎ የአንድ የሰብል ዘመን ሙከራ የባህርይ ልየታ ፍተሻ እንዲደረግበት ዝርያው ለመጣበት ክልልና ቀረቤታ ላለው አግባብነት ያለው የግብርና ምርምር ማዕከል ይልካል፣

ሠ) ዝርያው በሙከራ ሂደት ውስጥ አልፎ ሪፖርት ሲቀርብ መረጃዎችን አጠናክሮ ለዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፣

ረ) ኮሚቴው በቀረበለት መረጃ መሠረት ዝርያውን ሲያጸድቀው አስፈላጊውን መረጃ በመመዝገብ ለምርት እንዲውል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪/ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ፡-

በመደበኛ ሥርዓት ውስጥ እየሠራ የሚገኘው የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ካለበት መደበኛ ተግባር በተጨማሪ ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት እንዲካተቱ

የሚቀርቡትን ዝርያዎች በመገምገም በሥርዓቱ ዝርያ መዝገብ ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ሥርዓት /National Agricultural Research System/:-

ሀ) በመደበኛ የማዳቀል ሥርዓት ውስጥ ዝርያዎችን ያዳቅላል፣ ይመርጣል፣ የተሻለ ባህርይ ያላቸውን ለዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ አቅርቦ ወደ ልማት እንዲገቡ ያፀድቃል፣

ለ) በአርሶ አደሩ እጅ የሚገኙ የተሻለ ባህርይ ያላቸውን አካባቢያዊ ዝርያዎች ባህርይ ይገመግማል፣ ከዝርያዎቹ ባለቤት ጋር በመሆን በዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ በኩል እንዲመዘገቡ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ) አርሶ አደሩን ያሳተፈ የዝርያ መረጣ ሥራ አካሂዶ በጋራ ይገመግማል፣ በአርሶ አደሩ ተመራጭ የሆኑ ዝርያዎችን ያስለቅቃል፣

መ) የተለቀቁ/የተመዘገቡ ቴክኖሎጂዎችን በአርሶ አደር ማሣ ወይም በአርሶ አደሩ ማሠልጠኛ ማዕከላት ማሣ ላይ በመዝራት ያስተዋውቃል፣ ቅድመ-ኤክስቴንሽን ሥራ ያካሂዳል፣

ሠ) የዝርያዎቹን ዘር የቅድመ-ብዜት ሥራ በማከናወን የመነሻ ዘሮችን አባዝቶ ለዘር አባዥ ተጠቃሚው ያደርሳል፣

ረ) ለሚመለከታቸው አካላት ቴክኖሎጂዎቹን በተመለከተ ሥልጠና ይሰጣል፣

ሰ) ጥራቱ ለተገለጸ ዘር የተመዘገቡ ዝርያዎችን የሚጠብቁ ግብርና ምርምር ማዕከላትን ይወሰናል፡፡

፬/ የግብርና ሚኒስቴር እና የክልል ግብርና ቢሮዎች የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች፡-

ሀ) በሀገሪቱ የዘር ፍላጎት ላይ በመመርኮዝ ሊሠራጭ የሚችለውን ጥራቱ የተገለጸ ዘር መጠንን ይወስናል፣

ለ) ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት ውስጥ በአምራቾች መካከል ያለው የዘር አመራረት ቅንጅታዊ አሠራር እንዲሳለጥ ያደርጋል፣

ሐ) በየክልሉ ውስጥ ለሚካሄደው ጥራቱ የተገለጸ ዘር ግብይት የሥርጭት አካባቢዎችን ይወስናል፡፡

፫/ የክልል የግብርና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር አካላት

በክልሉ ጥራቱ የተገለጸ ዘር ለማምረትና ለማሠራጨት የሚፈልጉ አምራች ቡድኖችና ኀብረት ሥራ ማኅበራት ለመመዝገብ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ) በዚህ ሥርዓት መሠረት ለማምረት ሲፈልጉ ጥያቄያቸውን በተዘጋጀው ፎርም መሠረት አስሞልቶ ያስተናግዳል፣

ለ) ሊያመርቱት የሚፈልጉት ዝርያ ጥራቱ በተገለጸ ዘር መዝገብ መስፈሩን ያረጋግጣል፣

ሐ) በብቃት ማረጋገጫ መመሪያ መሠረት ተፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸውን የክልል ኢንስፔክተር ልኮ ያረጋግጣል፣

መ) በቀረበው የኢንስፔክተር ሪፖርት መሠረት አምራቹ ተፈላጊውን መስፈርት ማሟላቱ ሲረጋገጥ የብቃት ማረጋገጫ ሠርትፊኬት ይሰጠዋል፣

ሠ) የዘር አምራቾቹን ዕቅድ እና በጂ.ፒ.ኤስ የተደገፈ አድራሻ ተቀብሎ ለማሳው ወደሚቀርብ የዘር ጥራት ፍተሻ ማዕከል ይልካል፡፡

፬/ የክልል የዕፅዋት ዘር ላቦራቶሪዎች

ሀ) ከክልል የተላከላቸውን መረጃ መሠረት በማድረግ የአምራቹ ማሣ ጥራቱ ለተገለጸ ዘር ማምረት የሚውል መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ) አምራቹ የጠየቀው ዝርያ ጥራቱ በተገለጸ ዘር መዝገብ ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ሐ) በተገቢው የሰብል የዕድገት ደረጃ ወቅት ኢንስፔክተሩ ቢያንስ 10 በመቶኛ ወካይ የሆኑ ማሣዎችን በመምረጥ የመስክ የጥራት ቁጥጥር ያካሂዳል፡

መ) አምራች ቡድኑን ወይም ማኅበሩን የሚወክል ግለሰብ በጉብኝቱ ወቅት እንዲገኝ በማድረግ በሂደቱ የታዩ ጉድለቶች ማሟው ከማበቡ በፊት እርምት እንዲወሰድ ያደርጋል፣ በጥራት ማነስ ሊወድቅ ወይም ተገቢውን ደረጃ በማሟላቱ ሊያልፍ የሚችለውን ማሣ ያሳውቃል፣ ተገቢውን ቅጽ ሞልቶ ያስፈርማል፣

ሠ) ተቀባይነት አግኝቶ ካለፉ ማሣዎች ተመርቶ ከተዘጋጀለት ሎት ናሙና ይወስዳል፣ የላቦራቶሪ ፍተሻ ያደርጋል፣ የዘር ጥራት ውጤት ማረጋገጫ ሠርትፊኬት ይሰጣል፣

ረ) በመስክና በላቦራቶሪ ጥራት ውጤቶች ላይ የግብረ-መልስ ሪፖርት ለአምራቾችና ለሚመለከታቸው አካላት ይልካል፣

ሰ) የዘር ጥራት አጠባበቅን በተመለከተ ከክልሉ ጥራት ተቆጣጣሪ አካል ጋር በጋራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

፯/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲዎች፣ ቢሮዎች፣ መምሪያዎችና ጽ/ቤቶች፡-

ሀ) ይህን መመሪያ ዘር አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ተግባራዊ እንዲያደርጉት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፡

ለ) የዘር አምራች የኅብረት ሥራ ማኅበራት በወጣው መመሪያ መሠረት ተግባራቸውን እያከናወኑ ስለመሆኑ ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሐ) የመመሪያውን ተግባራዊነትና ክፍተቶች በጥናት ይለያል፣ ለፌዴራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ያሳውቃል፣ መሻሻል ካስፈለገ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መመሪያውን የማሻሻል ሥራ ይሠራል፣

መ) ኅብረት ሥራ ማኅበራት በመመሪያው መሠረት ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ የሚያደርጉዋቸው ማነቆዎችን በመለየት የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፣

ሠ) ስለመጋዘን አያያዝና የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ፡-

- ለኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላትና ሥራ አመራር አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል፣

ረ) የጥራት ደረጃው የተገለጸ ዘር የሚያመርቱ ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና አባላት ወደ መደበኛው የዘር አምራችነት መሸጋገር እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

ሰ) የተመረተው ምርት በአግባቡ እንዲሠራጭ የትስስር ሥራዎችን ይሠራል፣

ሸ) ኅብረት ሥራ ማኅበራት በጥናት ላይ የተመሠረተ ምርት አቅደው ማምረት እንዲችሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

፰/ ከክልል እስከ ወረዳ ግብርና እስከ ቀበሌ ያለው መዋቅር በተዋረድ የሚገኙ የግብርና መዋቅሮች፡-

ሀ) ዘር ለሚያመርቱ ኅብረት ሥራ ማኅበራት የተዘጋጀውን መመሪያ ተፈጻሚነት ይከታተላል፣ በተግባር ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮችን ይለያል፣ እንዲሻሻሉም ካስፈለገ መነሻ ሀሳብ ያቀርባል፣

ለ) በምርታማነታቸው የተመሰከረላቸው የዝርያ ዓይነቶች በአምራቹ አካል እንዲታወቁ ያደርጋል፣

ሐ) በማሣ መረጣና ዝግጅት ወቅት እንዲሁም በዘር ወቅት ለዘር አምራቾች አስፈላጊውን የኤክስቴንሽን የሙያ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

መ) ከአምራቹ ውጪ የሚደረጉ የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ከመከናወናቸው በፊት አምራቾቹ የውስጥ ቁጥጥራቸውን አከናውነው ዝግጁ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

ሠ) የዘር ፍላጎት መጠን አስቀድሞ ለህጋዊ ዘር አባዥ አካላት ያሳውቃል፣

ረ) የተመረተው ምርት ሲያድር በአርሶ አደሩ በአግባቡ እንዲያዝና ጥቅም ላይ እንዲውል ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

ሰ) የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ኮሚቴ እንዲቋቋም ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ እንዲሁም የውስጥ ቁጥጥር ሥራ ድጋፍ ይሰጣል፣

፱/ ጥራቱ የተገለጸ ዘር አምራች

ሀ) አስፈላጊውን የዘር ጥራት ቁጥጥር አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ ያቀርባል፣

ለ) ጥያቄው ተቀባይነት ሲያገኝ የዘር ማምረቱ ሥራ ጥራቱ የተገለጸ ዘርን የጥራት መስፈርት መሠረት አድርጎ ያከናውናል፣

ሐ) በመስክ ደረጃ የዘር ጥራት ቁጥጥር (ኢንስፔክሽን) ከተደረገ በኋላ ሊወገዱ/ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮችን ተከታትሎ ይፈጽማል፣

መ) የጥራት ቁጥጥሩን ያለፉ ማሳዎች ሰብልን ለመሰብሰብ ትክክለኛው የዘር እርጥበት መጠን ደረጃ መድረሱን ያረጋግጣል፣

ሠ) የጥራት ደረጃን ሳያሟሉ ከወደቁ ማሣዎች ዘር እንዳይሰበሰብ ኃላፊነት ወስዶ ይሠራል፣

ረ) ተቀባይነት ካገኙ ማሣዎች ዘር በወቅቱ ሰብስቦ የውቂያ ተግባራትን ይፈጽማል፣

ሰ) የተወቃውን ዘር አበጥሮ በተገቢ ከረጢት ያሽጋል፣ የሎት አደራደርን ተከትሎ ያከማቻል፣

ሸ) ክምችቱን ተከትሎ ናሙና እንዲወሰድለት ማሣዎችን ይከታተል ወደነበረው የዘር ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ጥያቄ ያቀርባል፣

ቀ) ለዘርነት እንዳይውሉ በላቦራቶሪ ውሳኔ የተሰጠባቸውን የዘር ሎቶች በሥርጭት ሥርዓቱ እንዳይካተቱ ኃላፊነት ወስዶ ይሠራል፡፡

፲/ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

ሀ) ጥራቱ የተገለጸ ዘር አምራች ማኅበራትን ወይም ቡድኖችን አቅም በቢሮ፣ በላቦራቶሪ መገልገያ መሣሪያዎች፣ በዘር ማበጠሪያዎች ሙያዊ ሥልጠናና በሌሎችም አቅማቸው እንዲጎለብት እገዛ ያደርጋሉ፣

ለ) ጥራቱ በተገለጸ የዘር ሥርዓት ላይ በገበያ ትስስር በኩል እገዛ ያደርጋሉ፡፡

፲፩/ ስለቅሬታ አቀራረብ

ሀ) ይህንን መመሪያ መሠረት ተደርጎ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚመለከተው የክልሉ ባለሥልጣን መ/ቤት ማቅረብ ይችላል፣

ለ) ማንኛውም ሰው በክልል ባለሥልጣን የተሰጠው ውሳኔ ካላረካው ቅሬታውን ለሚመለከተው የፍትህ አካል በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፣

፲፱/ ወንጀሎችና ቅጣቶች፣

ማንኛውም ሰው፡-

- በዚህ መመሪያ መሠረት ያልተመዘገበ እና የጥራት ቁጥጥር ያልተደረገበት ወይም የኢትዮጵያን ጥራቱ የተገለጸ የዘር ደረጃ መስፈርቶችን የማያሟላ ዘር ለገበያ ያቀረበ፣
- በዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ግብይት ወይም የጥራት ቁጥጥር ሂደት እንዲፈጸም መደለያ የሰጠ እንደሆነ ወይም፣

ማንኛውም ሰው፡-

- የተሳሳተ የዘር ናሙና ለምርመራ ያቀረበ፣
- በዚህ መመሪያ መሠረት የተወሰደን ማንኛውንም ናሙና የቀየረ፣

በዚህ መመሪያ መሠረት ማንኛውንም ማመልከቻ ሲያቀርብ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ፣ የተሰጠን የምስክር ወረቀት፣ የመለያ ምልክት ወይም ሌላ ህጋዊ ሠነድ የለወጠ፣ የደለዘ ወይም ያጠፋ እንደሆነ በዘር አዋጅ ቁጥር 782/2005 ባወጣው የወንጀለኞችና ቅጣቶች ህግ መሠረት ይቀጣል፡፡

**መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ ሺ ፯ ዓ.ም

ተፈራ ደርበው

የግብርና ሚኒስትር